ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
Re'ese Adbarat Debre Selam Kidest Mariam
Ethiopian Orthodox Tewahido Church

*"እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ፤ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁአቸው የአሕዛብ ደቀመዛሙርት አድርጓቸው።" ማቴ ፳፰፣ ፲፱*
*"Therefore go and make disciples of all nations, baptizing them in the name of the Father and of the Son and of the Holy Spirit," Matthew 28:19*

የባለአደራዎች ቦርድ ጽ/ቤት /OFFICE OF THE BOARD OF TRUSTEES

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::
In the name of the Father, the Son, and the Holy Spirit, Amen

መስከረም ፪ ቀን ፳፻፱ ዓም/ SEPTEMBER 9, 2016

# በዝርወት ከምትገኛው ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዋሽንግተን ዲሲ
# የ SEPTEMBER 9, 2016 ፍርድቤት ሂደት አስመልክቶ የተሰጠ ማብራሪያ

የተከበራችሁ የርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አባላት እና ወዳጆች በሙሉ
እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ አሸጋገረን። መጭውን ዘመን የሰላም የፍቅርና የአንድነት ያድርግልን።

እንደሚታወቀው ሁሉ አርብ ጳጉሜ ፬ ቀን ፳፻፰ ዓም (September 9, 2016) በቤተክርስቲያናችን ጉዳይ የፍርድቤት ቀጠሮ እንደነበረን ይታወቃል። በእለቱ የተከናወነውን ሂደት ጠቅለል ባለ መልኩ ነጥብ በነጥብ እንደሚከተለው እናብራራለን።

በመጀመርያ ዳኛው በችሎታቸው እንደተቀመጡ አንዳንድ ሃሳቦችን አቅርበው ጠበቃችንን Mr. Georgeን ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ጠየቋቸው። ጠበቃችንም ተነስተው በመጀመርያ ለተከበሩት ዳኛ ባለፉት ሳምንታት በወሰኑት ወሳኔዎች ላይ ይግባኝ እንደምንል አሳወቋቸው። ከዚህ በመቀጠል ዳኛው ጠበቃችንን ምን ላድርግልህ ብለው ሲጠይቁ፤ በእርሶዎ ችሎት permanent injunction ላይ ክሱ እንዲቀጥል በጠየቁት መሠረት የክሱ ሂደት በዚህ ሁኔታ እንዲቀጥል ዳኛው ተስማምተዋል።

**ትርጉም**

Temporary restraining order(TRO):- ችግር ፈጣሪ ግለሰብን(ግለሰቦችን) ክሱ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በአካባቢው እንዳይደረሱ ለማድረግ የሚቀርብ የክስ ጥያቄ።

Preliminary injunction:- ፍርድቤቱ የዋናውን ክስ በሚያይበት ጊዜ በህገውጥ ቦታውን የያዘው አካል እንዲወጣ ተደርጎ ህጋዊው አካል ንብረቱን ተረክቦ እያስተዳደረ ተከሳሽ አካል ከውጭ ሆኖ እንዲከራከር ለማድረግ የሚቀርብ የክስ ጥያቄ። **{ይሄ ዳኛው ውድቅ ያደረጉብን ጥያቄ ስለሆነ በይግባኝ የምንጠይቀው ጉዳይ ነው።}**

Permanent injunction:- ዘለቄታዊ ፍትህን በማግኘት ተከሳሽ አካል ሁለተኛ በከሳሽ ንብረት ላይ ማናቸውም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄ እንዳያቀርብ ለማድረግ የሚቀርብ የክስ ጥያቄ ነው።

በመቀጠልም የተካሄደው ደግሞ የተከሳሾች ጠበቃ የተለያዩ የውሳኔ ሃሳቦች እንዳሏቸው አቀረቡ። እነኝህን ለውሳኔ የቀረቡ ነጥቦችን ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር እነሆ፤

## 1. <u>የባለአደራዎች ቦርድ ምርጫን በተመለከተ</u>

የተከሳሾች ጠበቃ ዳኛው ያላቸውን ሃይል ተጠቅመው በፍርድቤቱ የተወከለ ሰው ባለበት ምርጫ እንዲካሄድ እንዲያዙ ጠየቁ። የተከበሩት ዳኛ ግን እናንተ በስምምነት ማድረግ ካልቻላችሁ እኔ አልገባበትም በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ አድርገውታል።

2. <u>**ክሱን ውድቅ ስለማድረግ**</u>(Permanent injunction)

በህገ ወጥነት የያዙትን ቤተክርስቲያን ለቀው እንዲወጡ እንዲደረግልን ያቀረብነውን ክስ ውድቅ እንዲያደርጉ የተከሳሽ ጠበቃ ላቀረቡት ጥያቄ የተከበሩ ዳኛ እንደማይቀበሉት ግልጽ አድርገዋል።

## 3. <u>የጥሬ ገንዘብን በተመለከተ</u>

( EAGLES BANK ) በኢግልስ ባንክ የተቀመጠውን ከሶስት ሚልዮን ዶላር በላይ የሆነውን ገንዘብ እንዲለቀቅላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ የተከበሩት ዳኛ ውድቅ ሲያደርጉባቸው፤ የቤተክርስቲያናችን መስራች ለሆኑት ለአቶ ካህሴ ወንዳፈራሁ እንዲለቀቅላቸውና እሳቸው እንዲያስተዳድሩ ቢጠይቁም ጠበቃችን ባሰሙት ተቃውሞ መሰረት ወድቅ ተደርጓል።


## 4. <u>$300,000.00ሺ ዶላር በተመለከተ</u>

የባለ አደራው ቦርድ ለአባላቱ ከአሁን በፊት ግልጽ እንዳደረገው ሁሉ ክሱ በተመሰረበት ጊዜ ይሄንን ገንዘብ አውጥቶ በተለየ ባንክ ውስጥ አስቀምጦ እንደነበር ይታወሳል።ይሄንንም አካውንት ተከሳሾች ባደረሱት ተጽእኖ መታገዱን አስታውቀን ነበር። የተከሳሾች ጠበቃ ይሄንን ገንዘብ ያለአግባብ እያባከነ በመሆኑ ካለበት ባንክ ወጥቶ ወደ ኢግልስ ባንክ እንዲዘዋር ቢጠይቅም ጠበቃችን ለተከበሩት ዳኛ ገንዘቡ በማይንቀሳቀስ በታገደ አካውንት ወስጥ መሆኑ ሲነገራቸው ዳኛው ገንዘቡ ባለበት እንዲቆይ በማዘዝ ጥያቅያቸውን ውድቅ አድርገውታል።

በመጨረሻም ዳኛው የፍርድ ቤቱን ቀጠሮ ለ July/2017 በመቅጠር  በዕለቱ ችሎት አሰናብተውናል። ምንም እንኳን ረጅም ቀጠሮ ቢመስልም ከዚህ ዓመት ጀምሮ ጠበቆቻችን ብዙ የሚሰሩት ነገር እንዳለ ከዚህ በታች በገለጽነው የፍርድ ቤቱ ድሕረ ገጽ አድራሻ በመሄድ የተቀመጠው መረጃ በማገንበብ እራሳችሁ ሃቁንና እውነቱን ማግኘትና መረዳት ትችላላችሁ። ማወቅ የሚገባን እርግጠኛ ቀን ቀጠሮ ስላልተሰጠ ቀኑ እንደደረሰን ሂደቱን የምናስታውቅ መሆኑን እንገልጻለን።

"እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል።"

https://www.dccourts.gov/cco/maincase.jsf




Last name HABTE First Name: AKLILU

የተሰጠውን ስም በትክክል በማስገባት አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንደምትችሉ እናስታውቃለን።